## በፌስ-ቡክ መድረካችን ላይ፡

## ከአቶ ወንጌል ያሸንፉል አፈወርቅ አላሮ የቀረበ መልእክት፡-

የአዲስ ዓመት መልዕክት..........አዲስ ዓመት ሲመጣ አብዛኛው ሰው አዲስ እና መልካም ነገር....ሰላም.....ፍቅር.......ጤንነት......ብልጽግና ልማትን ይመኛል.......እግዚአብሔር የተናገራቸው የተስፋ ቃላት እንዲፈጸምለት ይመኛል........ነገር ግን እነኚህን የተዘረዘሩ ነገሮችን ለማግኘት ማሟላት ያለብን መስፈርቶች አሉ...........በሕይወታችን የሚነሳው ማዕበል ጸጥ ብሎ ሰላማዊ ኑሮ ለመኖር ዮናሳዊነትን (ለእግዚአብሄር ያለመታዘዝን) ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ አውጥተን መጣል አለብን (ዮናስ 1)..........እግዚአብሔር ለኛ የተናገረውን የተስፋን ቃል ለመጨበጥ ከሎጥ መለየት የግድ ይላል.......ሎጥ ጊዜያዊ ጥቅምን የፈለገ ራስ ወዳድ ሰው ነበረ፡፡(ዘፍ 13) አካናዊነትን ማስወገድ አለብን.........አካን ሌባ የነበረ ሰው ነው.......የስውር ኃጢዓት ሰርቶ እስራኤላዊያን በጠላቶቻቸው እንዲሸነፉ ያደረገ ሰው ነው.....አካን በሰራው ኃጢዓት ምክንያት 36 ሰዎች ሞቱ (ኢያሱ 7).........የቃየንን መንፈስ ማስወገድ አለብን.........ቃየን በቅናት ተሞልቶ ወንድሙን የገደለ ሰው ነው(ዘፍ 4).......በሥጋዊ ቅናት ከተሞላህ የእግዚአብሔር መንፈስ ካንተ ላይ ይርቅብሃል....በፈንታው እርኩስ መንፈስ መጥቶ ያሰቃይሃል.......ሳኦል ሥልጣኑን ዳዊት ይወስድብኛል በማለት በሥጋዊ ቅናት ተሞልቶ ዳዊትን ሲያሳድድው እርኩስ መንፈስ መጥቶ ሲያሰቃየው ነበር (1ኛ ሳሙ 16) ስለዚህ በሥጋዊ ቅናት ከተሞላህ ተቀበዝባዥና ተንከራታች ሆነህ ትቀራለህ........የእግዚአብሔር መንፈስ ከራቀብህ ሳይሳካልህ መቃብር ትወርዳለህ........ስለዚህ ውድ የፌስቡክ ጓደኞቼ እግዚአብሔር መልካም አምላክ ነው.......ስለዚህ እኛም በመልካም መንፈስ መሞላት አለብን........ዳንኤልም መልካም መንፈስ ስላለው ከአለቆችና ከመሳፍንት በለጠ ይላል የእግዚአብሔር ቃል (ዳንኤል 6) ስለዚህ በልጠህና ተሽለህ ለመገኘት በእግዚአብሔር መንፈስ መሞላት አለብህ........የድብልቅ ኑሮ መኖርም ለዘላቂ ስኬት አያበቃም.........መልዕክቴን ሳጠቃለል በዘላቂ ስኬት የተሞላ ኑሮ ለመኖር እግዚአብሔርን መታዘዝ.....እርሱን መፍራት........እርሱን መምሰል........ሳናቋርጥ መጸለይ...........መጽሐፍ ቅዱስን ሁልጊዜ ማንበብ.......የወንጌልን ሥራ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት........ለሰው ልጅ ሁሉ መልካምን ማድረግ........ለእግዚአብሔር ነገር ቅድሚያ መስጠት እና........ቅድስና.......አንኳር ነጥቦች ናቸው..........መልካም አዲስ ዓመት!!!.!.!

**ከአቶ ወንጌል ያሸንፋል አፈወርቅ አላሮ ለቀረበው፡ ለዚህ መልእክት፡ ከኢእመ የተሰጠ ትችታዊ መልስ፡-**

# "ዮም ፍሥሓ ኮነ!

**"በእንተ በዓለ ልደተ-ፍጥረት!**
**"በእንተ ልደተ ኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር!**
**"በእንተ ልደተ ትስብእታ፡ ዘእግዝእትነ፥ ወመድኃኒትነ ድንግል ማርያም!**
**"በእንተ ልደተ ትስብእቱ፡ ዘእግዚእነ፥ ወሰላምነ ኢየሱስ መሲሕ!"**

ይድረስ፡- ለአቶ ወንጌል ያሸንፋል አፈወርቅ አላሮ!

የአዲስ ዓመት መልእከትዎ፡ እውነተኛ ሃይማኖታዊ ልቦናን፡ በተመሥጦ፡ ጠልቆ የሚነካ፡ መልካም ስለኾነ፡ "የኢትዮጵያና የፍጥረቱ ኹሉ አምላክ፡ እግዚአብሔር ይስጥልን!" ብለን መርቀንዎታል።

በመልእክትዎ ውስጥ፡ *"..........እግዚአብሔር ለኛ የተናገረውን የተስፋን ቃል ለመጨበጥ ከሎጥ መለየት የግድ ይላል.......ሎጥ ጊዜያዊ ጥቅምን የፈለገ ራስ ወዳድ ሰው ነበረ፡፡(ዘፍ 13)"* ስለሚለው አስተያየትዎ ግን፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ ያለውን ሃይማኖታዊ አቋም፡ ግልጽ ልናደርግልዎ እንወድዳለን።

በእርስዎ በኩል፡ ለሎጥ፡ ይህን የመሰለ የተዛባና ተፃራሪ የኾነ የግብር ስም የሰጡት፥ ምናልባት፡ ሎጥ፡ ከአብርሃም የመለየቱን ጠንቅ፡ ምክንያት አድርገው ከኾነ፡ ለዚህ ምክንያቱ፡ ሎጥ ሳይኾን፡ የእርሱ እና የአብርሃም በኾኑት እረኞቻቸው መካከል፡ በየከብቶቻቸው መሠማሪያ ግጦሽና ማጠጫ ምንጮች ሽሚያ የተነሣ፡ በየጊዜው እየደረሰ በነበረው ያልተቋረጠ ግጭት መኾኑን፥ እንዲያውም፡ ይህን ኹኔታ ብቻ ሳይኾን፡ የመለያየቱን አሳብ ጭምር ያቀረበው፡ አብርሃም እንጂ፡ ሎጥ አለመኾኑን፡ ራስዎ ያመለከቱት፡ የብሉዩ መጽሐፍ ጥቅስ፡ እንዲህ ሲል ያረጋግጣል፡-

**"ወይቤሎ አብራም፡ ለሎጥ፡- 'ኢይኩን ጋእዝ፡ ማእከሌየ፤ ወእማእከሌከ። ማእከለ ኖሎትየ፤ ወወማእከለ ኖሎትከ፤ እስመ አኀው ንሕነ። ወናሁ፡ ኵላ ምድር፡ ቅድሜከ ይእቲ፤ *ተሌለይ እምኔየ!* እመ የማነ፡ አነ፣ ወአንተ፡ ጸጋመ፤ ወእመ አኮ፡ አንተ፡ የማነ፡ ወአነ፡ ጸጋም።**

"አብራምም፡ ለሎጥ፡ እንዲህ አለው፡- 'በአንተ እና በእኔ መካከል፥ በእረኞችህ እና በእረኞቼም መካከል፡ ፀብ አይኑር! እኛ፡ ወንድማማች ነንና። እነሆ፡ ምድር ኹሉ፡ በፊትህ ናት፤ *ከእኔ ተለይ!* እኔ፡ በቀኝ ብኾን፡ አንተ፡ በግራ፤ ያለዚያም፡ አንተ፡ በቀኝ ብትኾን፡ እኔ፡ በግራ እኾናለሁ። (ኦሪት ዘልደት [ዘፍጥ.] ፲፫፥ ፰-፱።)

ይልቁንም፡ አብርሃምና ሣራ፡ በቅድስት ሥላሴነቱ የተገለጠላቸውን፡ እግዚአብሔርን፡ በድንኳናቸው ውስጥ፡ በእንግድነት ተቀበለውና አስተናግደው በሚሸኙበት ጊዜ፡ በአንድ ወገን፡ ሎጥና ቤተሰቡ ይኖሩባቸው በነበሩት፡ በሰዶምና በገሞራ ከተሞች ላይ ሊደርስ ስለተዘጋጀው፡ ስለመለኮታዊው የፍርድ አፈጻጸም፡ እግዚአብሔር አብወእም፡ ምሥጢሩን ገልጸው፡ ለአብርሃም እየነገሩት ሣለ፣ በሌላው ወገን ደግሞ፡ እግዚአብሔር ወልድ እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ ኹለት መላእክትን ተመስለው፡ ወደሰዶምና ገሞራ ከተሞች ኼደው፡ በከተሞቹ ውስጥ የሚኖሩት ሕዝቦች በሙሉ፡ በኃጢአታቸው ጽዋ መሙላት የተነሣ፡ ከሰማይ በወረደ እሳትና ዲን፡ የመጥፋታቸው ዕድል ፈንታ፡ አግባብ መኾኑን አረጋግጠው፡ ፍርዳቸውን እንዲቀበሉ ያደርጉ በነበረበት ጊዜ፡ ሎጥ ብቻ፡ ኹለቱ ሴቶች ልጆቹ ጭምር፡ ከዚያ የጥፋት እሳት መዳናቸው ይታወቃል።

ያም የኾነው፡ ከዚያ፡ እጅግ ቀደም ብሎ ከደረሰው የጥፋት ውኃ እንደተረፉት፡ እንደኖኅና ቤተሰቡ ኹሉ፡ እንዲሁ፡ ሎጥና ኹለቱ ሴቶች ልጆቹም፡ በሃይማኖት ህልውናቸውና በምግባር ሕይወታቸው፡ እውነተኞች [ጻድቃን] ኾነው፡ አካኼዳቸውን፡ ከእግዚአብሔር ጋር በማድረጋቸው መኾኑ ታምኖበታል።

ስለዚህ፡ ሎጥ፡ ከዚህ፡ ከእርስዎ ከተሠነዘረበት ወቀሳ፥ ነቀፌታና ክስ፡ ፍጹም ነጻ እንጂ፡ ሰለባ መኾን አይገባውም።

ባይኾን እንኳ፡ ይኸው፡ የወቀሳ፥ የነቀፌታና የክስ ጦርዎ፡ "**ወነጸረት ብእሲተ ሎጥ፡ ድኅሬሃ፤ ወኮነት፡ ሓውልተ-ጼው!**

"የሎጥም ሚስት፡ ወደኋላዋ ተመለከተች፤ የጨው ሓውልት ኾናም ቀረች!" ወደተባለባትና ለጥፋቱ እሳት ወደተዳረገችው፥ የልጆቹም እናት ወደኾነችው ሚስቱ ተነጣጥሮና ተወርውሮ ቢኾን ኖሮ፡ እንዴት ባማረና በሠመረ ነበር?

ነገር ግን፡ ባለመታደል፡ የተቃውሞ አጥቂነትዎ፡ የዘር ሓረጉ፡ የመለኮታዊው ቃል-ኪዳን ተቀባይ በመኾን፡ ለአምላክ እናት፡ ለድንግል ማርያም እና ለልጇ፡ ለእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ቅድመ-አያትነት የበቃውን፡ ነቢዩን ንጉሥ ዳዊትን ያስገኘችውን፡ ሩትን ባፈራው፥ ምንም በደል በሌለበት፥ በጻድቁ፡ የእግዚአብሔር ሰው፡ በሎጥ ላይ ኾኖ መታየቱ አስገርሞናል። (ዘልደት [ዘፍጥ.] ፲፱፥ ፳፮።)

\+ \+ \+